የሰበር መ/ቁ. 38041

መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ታደሰ ገ/መስቀል - ወኪል በላይነሽ ሽፋው ቀረበች

**ተጠሪዎች**፡- 1/ ሙሉጌታ ዘካርያስ

2/ ወ/ሮ አበቡ ገበያው

3/ መሐመድ ይማም - ወኪልም ነው ቀረበ

4/ ዘውዴ ይማም

5/ ወ/ሮ ሩቅያ ይማም

6/ ወ/ሮ ዘይነባ ይማም

7/ ወ/ሮ አሚናት ይማም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ያለ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የጉዳዩ ታሪክ እንደሚያመለክተው በውርስ ንብረት ክፍፍል መነሻነት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች በአንድ በኩል፤ ከሦስተኛ እስከ ሰባት ድረስ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በሌላ በኩል በመሆን ክርክር ከተደረገ በኋላ፤ በወቅቱ ከሣሾች የነበሩት ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች በአንደኛ እና በሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ አስወስነው የፍርድ ባለመብት ሆነዋል፡፡ ይህን ውሣኔ መሠረት በማድረግም የአፈፃፀም መዝገብ ያስከፈቱ ሲሆን፣ በዚህን ጊዜም አመልካችንም የአፈፃፀም ተከሣሽ አድርገውት እንደነበር እና ፍ/ቤቱ ግን አመልካች ተከሶ የተፈረደበት የፍርድ ባለእዳ አይደለም በማለት ከአፈፃፀም ክሱ ውጪ እንዳደረገው ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ለአንደኛ እና ለሁለተኛ ተጠሪዎች ገንዘብ አበድሮ የነበረ በመሆኑ እና የውርስ ሃብት ነው ተብሎ ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ቤትም በመያዣ ይዞ ስለነበር ይህን የብድር እና የመያዣ ውል መነሻ በማድረግ በአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን በመክሰስ ቤቱን እንዲረከብ በፍ/ቤት አስወስኖአል፡፡ አመልካች ይህን ውሣኔ ያሰጠው በ1993 ዓ.ም ሲሆን፣ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአንደኛ እና በሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ ያስወሰኑት በ1997 ዓ.ም እንደሆነ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

አመልካች በአፈፃፀም መዝገቡ ተጣምሮ መከሰሱን እንዳየ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ቤቱን በተመለከተ ያሰጡት ውሣኔ መኖሩን ስላወቀ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርቦ ክርክር ከተካሄደ በኋላ ቤቱ በመያዣ የያዘው ከመሆኑም በላይ፤ በፍርድም ለሱ ይገባል ስለተባለ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ ለተጠቀሱት ተጠሪዎች ሊሰጥ አይገባም በሚል ተወስኖለታል፡፡ በዚህም በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር መሠረት

ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ መሠረት ተሽሮአል፡፡ ከዚህ በኂላ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ መሠረት የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በአማራ ብ/ክ/መ/ ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ሲሆን፣ በስር ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በሚል ይግባኛቸው ሣይስተናገድ ቀርቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች እና አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን መልስ ሰጭ በማድረግ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች በመሻር አመልካች በቤቱ ላይ መብት የለውም፡፡ ቤቱ በተጠሪዎች መካከል ይከፋፈል በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ጥር 24 ቀን 1993 ዓ.ም በመ.ቁ. 14/93 ክርክር ባስነሣው ቤት ላይ የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ባልተሻረበት ሁኔታ የጠ/ፍ/ቤቱ በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር ሲመረምር በመ.ቁ. 14/93 ላይ የተሰጠውን ውሣኔ የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በመ.ቁ. 14/93 ጥር 24 ቀን 1993 ዓ.ም ባስወሰነው መሠረት ለክርክሩ መንስኤ በሆነው ቤት ላይ የፍርድ ባለመብት ሆኖአል፡፡ ውሣኔው የተሰጠው ከሱ ገንዘብ በተበደሩት እና ቤቱንም በመያዣ በሰጡት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ ይህ ፍርድ ለየትኛውም ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ አልተሻረም፡፡ ከሦስት እስከ ሰባት ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ይህን አመልካች በመክሰስ በቤቱ ላይ መብት አላገኙም፡፡ ከዚህ የተነሣም አመልካች ቤቱን ያስረክባቸው ዘንድ የሚያስገድዱበት ምንም የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በቤቱ ላይ ያገኘው በፍርድ ላይ የተመሠረተ የባለቤትነት መብት በተመሣሣይ ሁኔታ በፍርድ ሃይል እስካልተነሣ ድረስ ምን ጊዜም የቤቱ ባለቤት ሆኖ የሚቀረው አመልካቹ ነው፡፡

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በስር ወረዳ ፍ/ቤትም ሆነ በከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው አመልካችን የቤቱ ባለቤት ባደረገው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አልቀረበለትም፡፡ ቤቱ የአመልካች አይሆንም በማለት የወሰነው በይግባኝ ያልቀረበለትን ውሣኔ ተፈፃሚነት የሚኖረው ውሣኔ አይደለም የሚል ትችት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በመሠረቱ በሕግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ የሞራልን ወይም የሕሊናን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ ዋጋ አልባ ሆኖ እንዲቀር ማድረግ በየትኛውም መለኪያ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች በክስ እንደሌሎቹ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የውርስ መብት እንደነበራቸው ተመልክተዋል፡፡ ቤቱን ለብድር በመያዣነት ለአመልካች የሰጡትም በእነሱ እጅ ስለነበረ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ለምን እነሱ ብቻቸውን በመያዣነት ሰጡ ብሎ መጠየቁም አግባብ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በፊት አመልካች ቤቱን በፍርድ የሱ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በመሆኑም ሌሎችም የውርስ መብት አላቸው ስለተባለ ብቻ ያለምንም ሕጋዊ ምክንያት ፍርዱ ተፈፃሚ እንዳይሆን ወይም ማምከን አይቻልም፡፡ ሲጠቃለል የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 311/2000 ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡ የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡአቸው ትእዛዝና ውሣኔ ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ጥር 24 ቀን 93 ዓ.ም በመ.ቁ. 14/93 በተሰጠው ውሣኔ በቤቱ ላይ ባለመብት ስለሆነ ለተጠሪዎች ሊያስረክብ አይገደድም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፣፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ